## ሳምንታዊ ዜና (ሚያዝያ 26 ቀን 2009.ም)

**በቦረና ግጭት ተቀስቅሶ አንድ የወያኔ የዞን አስተዳዳሪ ተገደለ፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ከፍተኛ ባለሥልጣናት እየሸሹ መሆኑ ተጋለጠ፣ ከ600 በላይ መኮንኖችና የበታች ሹማመንት ያሉባቸው ፖሊሶች ከስራ ሊባረሩ መሆኑ ታወቀ፣ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) በወያኔው ዳኛ ዋስትና ተከለከለ፣ ሶስት የወያኔ ፖሊሶች ለምስክርነት ተዘጋጅተዋል፣ የ16ተኛው የአፍሪካ አትሌቲክስ መክፈቻ ሥነ ስርዓት በዓል ላይ ተቃውሞ ተነሳ፣ በርካታ ወጣቶች ታፍሰው ተወሰዱ፣ መለስ ዜናዊ ለተሰናባቹ አልፋ ኦማር ኮናሬ ውለታ መክፈያ ነው ተባለለትን ጠቀም ያለ ሽልማት ስጠ ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ዝርዝር ዜና ያንብቡ..............................**

ወያኔ በዘረጋው የዘረኛና የጐጠኛ ፖሊሲ ምክንያት በመላ ሀገሪቱ የሚቀሰቀስ የእርስ በእርስ ግጭት ከግዜ ወደ ግዜ እየተስፋፋ መምጣቱን ከተለያዩ አካባቢዎች ከሚደርሱን ዘገባዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

እንደደረሰን ዘገባ ከሆነ በቅርቡ ደቡብ ክልል ተብሎ በሚጠራው በቦረና ቦዳ ውስጥ በኦሮሞ ብሔረሰብና በሱማሌ ብሔረሰብ መካከል ወያኔ በረጨው የጎጠኝነት መርዝ የተነሳ ግጭት ተከስቶ በርካታ ሰዎች ሲሞቱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት አካባቢውን ለቅቀው እንደተሰደዱ አስረድቷል፡፡

ሚያዝያ 5ቀን 2000 ዓ.ም የተከሰተው ይኸው ግጭት ለ7 ተከታታይ ቀናት የሰነበተ ሲሆን የማቾቹ ቁጥር ለጊዜው አይታወቅ እንጂ በሁለቱም ወገን የሞተ እና የቆሰለ መኖሩን የገለፀው ዘገባ በተለይም የተሰደዱት ቁጥር እጅግ በርካታ መሆናቸውን ገልጿል፡፡

የሁለቱም ብሔረሰቦች ግጭት መንስኤ በቦታ ይገባኛል በሚል ሲሆን፣ ይህ ችግር እንዲከሰት ያደረጉት የወያኔ ካድሬዎች ሆነ ብለው እንደሆነ የገለፀው ዘገባው ለዘመናት የሁለቱ ብሔረሰብ ተወላጆች ተግባብተውና ተቻችለው በጋራ ሲጠቀሙበት የነበረውን የግጦሽ መሬት ለአንደኛው ብቻ ነጥሎ ከሰጠ በኂላ እንደገና መልሶም ለሌላኛው በመስጠት በአካባቢው ሠላም እንዳይኖር በማድረግ ሆን ተብሎ የታቀደው ተግባራዊ መሆኑን የገለፁት የአካባቢው ነዋሪዎች በአካባቢው ታጣቂ የተቃዋሚ ኃይሎች የሚንቀሳቀሱበት በመሆኑ እና የአካባቢው ሕዝብ በወያኔ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ያለው ስለሆነ ሁለቱን ብሔር አጋጭቶ በእነሱ መንደድና መቃጠል ከዳር ሆኖ ለመሞቅ የሰሩት ተንኮል ነው ሲሉም አሰረድተዋል፡፡

ወያኔ እራሱ በዘረጋው የጐጠኛ መንገድ ሕዝቡን እርስ በእርስ መልሶ ከሳሽ፣ ወቃሽ፣ አስታራቂ ለመሆን ቢዳክርም ሕዝቡ ቀድሞ በማወቁ የራሱን እርምጃ እየወሰደ ሲሆን በቅርቡም በዚሁ በሚያዝያ 5 ቀን 2000 ዓ.ም በተከሰተው የሁለቱ ብሔር ግጭትን ለመሸምገል ወደ ስፍራው የተጓዘውን በሱማሌ ክልል የሸንሌ ዞን ዋና አስተዳዳሪን የገደሉት መሆኑን የገለፁት ምንጮች ግለሰቡን መጀመሪያ ግጭቱ እንዲስፋፋ ከአለቆቹ የተሰጠውን ተልእኮ ከተወጣ በኂላ መልሶ ለማስታረቅ በተጓዘበት ወቅት እርምጃው እንደተወሰደበት ገልፀዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በደቡብ ክልል ውስጥ ባሉ ብሔር ብሔረሰቦች መካከል የእርስ በእርስ ሽኩቻ እንዲከሰት አድርጎ የብዙ ሰው ሕይወት እንዲጠፋና ለብዙ ሰዎች መቁሰልና በሺህዎች ለሚቆጠሩት ለመሰደድ እንደተገደዱ ሁሉ አሁንም ወያኔ የውስጥና የውጭ ፖለቲካው ድብልቅልቁ ወጥቶበት በመሆኑ ይህንኑ ለማስተንፈስ በሚል በተሳሳተ መንገድ ሕዝቡን እያጋጩ ነው ሲሉ አስተያየት የሚሰጡ የአካባቢው ነዋሪዎች በርካቶች ናቸው፡፡

በተመሳሳይ ወያኔ ዙሪያ ገባውን ግራ ሲገባው ቀድሞ በጀመረው የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲው ቀጥሎበት በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥም ተመሳሳይ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል፡፡

እንደደረሰን ዘገባ ከሆነ ወያኔ ስልጣን ላይ እንደተቆጣጠረ ለስርዓቱ ያገለግሉኛል ብሎ ያመነባቸውን ጥቂት ግለሰቦች ያለአቅማቸው ስልጣንና ኃላፊነት ሰጥቶ ግለሰቦቹ ሕዝቡን እንደልባቸው ሲያስሩና ሲያሰቃዩ የነበረ በመሆኑ ዛሬ ይህ ቁርሾ ሆኖ የተዳፈነው በመፈንዳቱ በበርታና ጉሙዝ ብሔረሰብ መካከል ትልቅ ችግር መከሰቱ ተገልጿል::

በቤንሻንጉል ክልል ውስጥ በርታና ጉሙዝ መካከል የተከሰተው ይኸው ግጭት ዛሬ ሳይሆን የቆየ መሆኑን ያስታወሰው ይኸው ዘገባው ወያኔ የበርታ ብሔር (ነገዶችን) እያሳደደ በጥይት ሲፈጃቸው የነበረ እና የጉሙዝ ተወላጆችን ደግሞ በስልጣን ላይ እያስቀመጣቸው እንደልቡ ሲጋልብባቸው የነበረ ቢሆንም በአሁን ወቅት የበርታ ብሔር ተወላጆች በወያኔ ላይ ባላቸው ከፍተኛ ጥላቻ እርምጃ እንወስዳለን ብለው በማስጠነቀቃቸው በርካታ የክልሉ ባለሥልጣናት እየሸሹ ወደመሀል ሐገር እየገቡ መሆኑን ገልጿል::

የወያኔ ቀንደኛ ተላላኪ ካድሬዎች ላይ እርምጃ እንወስዳለን ብለው በመግለፃቸው የደነገጡት ባለሥልጣናቱ ከሚያዝያ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ወደ አዲስ አበባ እየገቡ ሲሆን በምትኩ ግዙፍ ቁጥር ያለው ሠራዊት ወደ ስፍራው እየተጓዘ መሆኑን ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልጿል::

«አንቺው ታመጪው አንቺው ታሮጪው» እንዲሉ ወያኔ ለስርዓቱ እድሜ ማራዘሚያ ይሆኑኛል በሚል ብቻ ለዘመናት ተፋቅሮ የኖረው ሕዝብ እርስ በእርስ እያጋጨት እዚሁ ደረጃ የደረሰ ቢሆንም አሁን ሕዝቡ ሲነቃ ደግሞ መግቢያ መውጫያ አጥቶ የእውር ድንብሩን እየተሯሯጠ መሆኑን የገለፀው ይኸው የደረሰን ዘገባ የክልሉ ባለሥልጣናት በሕዝቡ እርምጃ ይወሰድብኛል በሚል ፍራቻ ብቻ በርካቶች ለቅቀው እንደወጡ በዝርዝር አስረድቷል::

የክልሉ የስራ ቋንቋ አማርኛ በመሆኑ በርካታ ምሁራኖች ወደ አካባቢው የገቡ ቢሆንም አሁን በተከሰተው የባለሥልጣናት ለቀቆ መውጣት የተነሳ ተደናግጠው በርካታ የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞች ለቅቀው ወደ መሀል ሃገር እየገቡ መሆኑን እና ስራ በአብዛኛው መስሪያ ቤት እንደተቋረጠ የደረሰን ዘገባ ገልጿል።ልማትናዲሞክራሲ የሰፈነባትየሚሊኒየሙን ህዳሴ የሚያረጋግጡባት እየተባለ ወያኔዎች የተናገሩት በወያኔኛ ቁዋንቁዋ በጎሳ ግጭት መተላለቅ በቅልብ ወታደር ሰላማዊ ዜጋን ጨፍጭፎ ማስገደል የሚል ትርጉም አለው እንዴ በማለት የሚጠይቁ መልስ ይፈልጋሉ እርግጥ ነው ያዲያቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም

በቅርቡ በሁሉም መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው አዲስ የሠራተኛ መቅር በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሠራተኛን ከስራ የሚያፈናቅል መሆኑ ታወቀ::

ለ25 ዓመታት እና ከዚያም በላይ ያገለገሉ ነባር የፖሊስ አባላትና በዚሁ ተደረገ በተባለው ቢ.ፒ.አር በተሰኘ ጥናት ምክንያት ከ600 በላይ መኮንኖችና የበታች ሹማምንት ከስራ ሊባረሩ መሆኑን የፌዴራል ፖሊስ የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ::

እንደ ምንጮቹ ገለፃ ከሆነ ለብዙ ዓመት ሲያገለግሉ የነበሩ እስከ ኮማንደር (ኮሎኔል) ማዕረግ ያላቸው መኮንኖችን ጨምሮ የኢንስፔክተር (ሻምበል) እና ሌሎችንም ከ600 በላይ የፖሊስ አባላት ለማባረር ዕቅድ ያለቀ በመሆኑ በአሁን ሰዓት በግዳጅ የዓመት ፈቃድ እንዲወጡ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል::

በተለይም ከፌዴራል ዋና መስሪያ ቤት ከማዕከላዊ ምርመራ መስሪያ ቤት ውሰጥ ብዙ ነባርና ልምድ ያላቸው ነገር ግን አቋማቸው ለወያኔ ባለሥልጣናት የማያስደስት ሆነው የታዩት መኮንኖችና ሹማምንቶች የዚሁ ሰለባ በመሆናቸው ሰሞኑን በግዳጅ ከስራ ፈቃድ እየተሰጣቸው

እንዲወጡ የተደረገ ሲሆን፣  በምትካቸው ስራውን እንዲሰማመዱ የተባሉ የወያኔ ካድሬ መኮንኖች እየሰሩ መሆኑን ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

ወያኔ በእሳት ላይ ቤንዚን እያርከፈከፈ እንደሚጫወተው የአእምሮ ሕመምተኛ ከጊዜ ወደ ጊዜ ውስጡ ያለውን የአረመኔነት ባህርይ እያጐላ አምጥቶ ሕዝቡ በኑሮ ውድነት እንዲጠበስ፣ በውሀ ችግር እንዲታመስ፣ በመብራት እጦት እንዲያለቅስ ከማድረጉ በተጨማሪ የመንግስት ሠራተኛውን ደግሞ መልሶ ከስራ ለማፈናቀል እየተሯሯጠ መሆኑ ሕዝቡን መናቅና ሐገርን ማውደም መሆኑን የገለፁት አንድ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ መኮንን አሁንም ወያኔዎች በነባሩ ሰራዊት ላይ ካላቸው ጥላቻ የተነሳ ብዙ እርምጃ ሊወስዱብን ይችላሉ ሲሉ ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል፡፡

ጥንቱኑ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስትን ጥዶ ማልቀስ እንዲሉ ህዝባዊ ወገንተኝነት ይበጃል ብለን መክረን ፣ዘክረን ነበር ዛሬ ወያኔ እንደፈለገ ተጠቅሞ እንደ አገዳ ሲተፋ ከማላዘን ቀድሞውኑ መብትን አስጠብቆ ፣ ለህዝብና ለሙያው ታማኝ መሆን ቢቻል ኖሮ ወያኔም አጉራ ዘለል ሆኖ ልቡ አብጦ አይፈነዳም ነበር ለማንኛውም ይህም ሆነ የቀረው አባልም ከሆዱ ወደ ህሊናው መመለስ አለበት ምክር የሚሰጡትን ወገኖች ሃሳብ የምንጋራው ይሆናል ያሉ አሉ

በሌላ ዜና ታዋቂው ድምፃዊ ቴዎድሮ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) በተከፈተበት  የፈጠራና የሀሰተኛ ክስ የዋስትና መብት አያሰጥም ሲል የወያኔው ቀንደኛ ካድሬ ዳኛ ልዑል ገ/ማርያም መከልከሉ ታወቀ፡፡

ከዚህ ቀደም  የቅንጅት መሪዎችንና ጋዜጠኞችን የሃሰት ክስ እንዲከታተል  የተሰየመው ችሎት የቀኝ ዳኛ የሆነው ይኸው ልዑል ገ/ማርያም የቴዲ አፍሮን የተቀነባበረ ሀሰተኛ የፈጠራ ክስ ለማየት ሲባል የ8ኛ ችሎት መሀል ደኛ ሆኖ የተሾመ ሲሆን፣ በተለይም  በቴዎድሮስ ስራዎች ላይ ባላቸው ጥላቻ  ብቻ አረመኔውን ዳኛ መድበው ማስቀጣታቸው ታውቋል፡፡

ቴዲ ማክሰኞ ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም ቀጠሮ ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም ወያኔው ልዑል ገ/ማርያም የተባለው ካድሬ የተከፈተብህ አንቀፅ ዋስትና ስለማያሰጥ ወደ ክርክሩ እንገባለን በሚል ለግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም ቀጠሮ  መስጠቱ ታውቋል፡፡

የቴዲ አፍሮ አድናቂዎች ፍርድ ቤቱን አጨናንቀው  የዋሉ ሲሆን  ቁጥራቸው ለጊዜው ያልታወቁትን ፌዴራል ፖሊስ ከፍርድ ቤትና ከውጭ እያፈሱ ወዳልታወቀ ስፍራ የወሰዱዋቸው ሲሆን፣ ብዙዎቹ ሴቶች እንደነበሩም ለማየት ተችሏል፡፡

በዕለቱ ቴዲ አፍሮን ካየ ሕዝቡ አያሳልፈንም በሚል ፍራቻ ብቻ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ከቃሊቲ አውጥተውት ከፍተኛው ፍርድ ቤት ያስገቡት ሲሆን እስከ ጠዋቱ 3 ሰዓት ድረስ ለተከታታይ 5 ሰዓታት  ያህል በትንሽዋ መኪና ውስጥ በብርድ እንዲጠበስ ተደርጎ እንደነበር ታውቋል፡፡

የሕዝብ ድጋፍ እና አመኔታ  የሌለው ወያኔ በ1997 ዓ.ም ባወጣው አልበሙ በወያኔ ሹማምንቶች ዘንድ ቂም የተቋጠረበት ሲሆን ከድርጊቱ ጋር ፍፁም በማይገናኝ መልኩ የሀሰተኛና የፈጠራ ክስ ተመስርቶበት ያለምንም ሀጢያት የዋስትና መብቱን ነፍገውት ወደ ዘብጥያ የመለሱት ሲሆን ቴዲን እንደ ደመኛ ጠላታቸው የሚመለከቱት የወያኔ ሹማምንቶች በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ ያሰሩት ከመሆኑም በላይ የሚነበብ አንዳችም ነገር እና ሬዲዮ እንዳይገባለት የተከለከለ መሆኑን የወህኒ ቤት ምንጮች ገልፀዋል፡፡

በሕዝብ እንዳሳለቅክብን እኛም እንቀልድብሃለን በሚል ያስፈራራው የእስር ቤቱ ዋና ኃላፊ አበበ ዘሚካኤል የተባለው የሕወሓቱ ሰው ዘመዶቹ እና ጓደኞቹ እንዳይጠይቁት የከለከለ ከመሆኑም

በላይ ቅዳሜና እሁድ እንደማንኛውም እስረኛ እንዳይጠየቅ ለግሉ ብቻ ፕሮግራም ወጥቶለት ከቀኑ 6 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት ለአንድ ሰዓት ብቻ እንደተፈቀደለት ገልፀው የሚገቡት ሰዎችም ከአራት የማይበልጡ ለዚያውም ቀድሙው የተመዘገቡትን 3 ዘመዶቹ እና ማናጀሩ ብቻ መሆኑን ገልፀዋል::

ቴዎድሮስ ካሣሁን በሚያወጣቸው በሳል ዘፈኖች ቋንቋውን በማይሰሙት የውጭ ሀገር ዜጎች ጭምር ዝናን ያተረፈ ወጣት አርቲስት ሲሆን አሁን የተከፈበት የፈጠራ ክስ እንዲሰረዝ በየጊዜው ወደ ፍርድ ቤት የሚመጡ አድናቂዎቹ በተቃውሞ እየገለፁ ሲሆን ማክሰኞ ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በተመሳሳይ ሁኔታ የቴዲ አፍሮን ምስል የያዘ ጥቁር ቲሸርት ከ70- እስከ 100 ብር ድረስ የተቸበቸበ ከመሆኑም በላይ ወጣቱ ቲሸርቱን ለብሶ በመሄዱ የተበሳጩት የወያኔ ፌዴራል ፖሊሶች ልብሱን የለበሱትን በሙሉ አፍሰው የወሰዷቸው መሆኑን የተመከተ ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ወደ ልደታ ፖሊስ ጣቢያ አስገብተው በጉማ እንደደበደቧቸውም አሰረድቷል::

የሀገርና የህዝብ ፍቅር የማያውቁት ከሕዝብ ጋር ሳይቀላቀሉ እንደ ዱር አውሬ ለብቻቸው በአንድ ቦታ ታሽገው የሚውሉት የፌዴራል ፖሊሶች እንደገድል የአለቆቻቸውን ትዕዛዝ ብቻ እያስተጋቡ ሕዝቡን ፍዳ እያበሉት ሲሆን፣ በዚያን እለትም እጅግ ከወትሮው በተለየ መልኩ ሲጉርፍ የመጣውን ሕዝብ በአራቱም አቅጣጫ እንዲመለስ ሙከራ ሲያደርጉ የነበረ ቢሆንም ሕዝቡ ለቴዲ ካለው ፍቅርና አክብሮት የተነሳ እያለፈ መግባቱንና በዚህም የተጨናነቁት ፖሊሶች መሳሪያ የታጠቀ ኃይል በሁለት አራል አምጥተው ሲያራግፉ ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ማየቱን በሪፖርቱ ገልፆ የታፈሱት ወጣቶች ለአንድና ለሁለት ቀን ከታሰሩ በኋላ «ሁለተኛ ፍ/ቤት መጥቼ ጉዳዩን አልከታተልም ይህንን ካደረግኩኝ የ3 ዓመት ቅጣት ይወሰንብኝ» በሚል ማስገደጃ ፎርም ተሰጥቷቸው በመፈረም እንደገና ሌላ ዋስ ሆኖ የሚያስፈታቸው ቤተሰብ እንዲመጣ እና እንደሚለቀቁ ተነግሮዋች ነበር ብሎል ::ይሁን እንጂ ይህ የዜና ዘገባ ትንታኔ ተጠናቅሮ እስከተዘጋጀበት ዛሬ እሁድ ሚያዝያ 26 ቀን 2000ዓ.ም ድረስ በቴዎድሮስ ካሳሁን ጉዳይ ፍርድ ቤትበመሄዳቸውብቻ ከታሰሩት ውስጥ ዋስትና ተከልክል ከእስር እንዳልወጡ ታቆዋል

የወያኔው ፍርድ ቤት ለግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም አቃቤ ህግ ተብየው የወያኔ ክንፍ የሰው ምስክሮችን ይዞ እንዲቀርብ የታዘዘ ሲሆን፣ በወቅቱ ያልነበሩ ነገር ግን ስለ ጉዳዩ እንዲያጠኑ የተደረጉ 3 ፖሊሶች እንደሚቀርቡ ለማወቅ ተችሏል::

በፈጠራ ክስ የተመሰረተበት ቴዲ አፍሮ በ1994 ጥቅምት ወር ጉዳዩን ሲያጣራ የነበረው ፖሊስ ሀሰት መሆኑን አረጋግጦ የለቀቀው መሆኑ እየታወቀ እንደገና ቴዲን ለመበቀል ሲሉ ብቻ 3 ፖሊሶችን አስጠንተው እንዲመሰክሩ ለማድረግ የተሰራው ተንኮልና ሴራ ነገ ታሪክና ትውልድ ፊት የሚያስጠይቃቸው መሆኑን የሚገልፁት አድናቂዎቹ በእንባ እየተራጩ እርስ በእርስ ሲተቃቀፉ እንደነበርም በስራፍው የነበረው ዘጋቢያችን አስረድቷል::

ቴዲ አፍሮን ለመጠየቅ የሚጓዘው ህብረተሰብ ቁጥር እጅግ በጣም ከመብዛቱ የተነሳ ቃሊቲ እስር ቤት እየተጨናነቀ ቢሆንም ቴዲን ግን ለማግኘት እንዳልቻሉ የሚገልፁት አድናቂዎቹ ህዝብ በነፃነት እንዳይጠይቅ ይህንን የመሰለ ጫና መፍጠራቸው በእጅጉ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲሉም በቁጭት ይገልፃሉ::

በቴዲ አፍሮ የዋስትና መብት መከልከል የበገነው ወጣት ረቡዕ ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም ከጠዋቱ 2 ሰዓት ጀምሮ በስታዲየም ዙሪያ ተሰባስበው ወያኔን ሲያወግዙ እንደነበር የአይን እማኞች ገለፁ::

በሌላ ዜና የ16ተኛው የአፍሪካ ሻምፒዮን በአዲስ አበባ ስታዲየም የተዘጋጀ ሲሆን፣ የመክፈቻውን ስነ ስርዓት በማስመልከት አምባሳደሮች ዲፕሎማቶች እንዲሁም ከተለያዩ ሀገራት የመጡ አትሌቶች ይገኙበታል ተብሎ በታሰበው በስታዲየም ዙሪያ ወጣቶች ወያኔን የሚያወግዝ መፈክር ሲያሰሙ እንደነበር የአይን እማኞች ገልፀው ሲቪል የለበሱ ደህንነቶችና የፌዴራል ፖሊሶች ወጣቶችን እያፈሱ በፒክ አፕ የፖሊስ ታርጋ በለጠፉ አራት መኪኖች መውሰዳቸውንም መመልከታቸውን ጨምረው ገልፀዋል።

አንድም ለሀገርና ለወገን ፍቅር የሌለው ወያኔ ለህዝብ ሀብትና ንብረት እንዳሻው ሲጫወትበት መላው የሀገሪቷ ህዝቦች በችግር እየተጠበሱ መሆኑን ለማስገንዘብ ወጣቶች መፈክር ሲያሰሙ የነበረ መሆኑን የገለፁት የአይን እማኞች ከ60 በላይ ወጣቶች እየተደበደቡ እንደተወሰዱና ከ3:30 በኋላ ቁጥራቸው እጅግ በርካታ ደህንነቶች በአካባቢው ሰፍረው መዋላቸውን ገልፀዋል።

በመጨረሻም በሀገርና በህዝብ ሀብት እየቀለደ ያለው ወያኔ በአፍሪካ ሕብረት ሊቀመንበር ሆነው ሲያገለግሉ ለነበሩት አልፋ ኦማር ኮናሬ ጠቀም ያለ ሽልማት መስጠቱን ለአፍሪካ ህብረት ጽህፈት ቤት ቅርበት ያላቸው ዲፕሎማቶች ገለፁ።

ለወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ቅርብ የሆኑት እኚሁ አልፋ ኦማር ኮናሬ በተለያዩ ጊዜ በሀገሪቷ ህዝብ ላይ ችግሮች ሲደርሱ ምንም እንደልተፈጠረ በማስመሰል ሽፋን ሲሰጡ የነበሩ ሲሆን፣ በተለይም በ1997 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ወያኔ ሙሉ በሙሉ በተሸነፈበትና በዚህም ሳቢያ ከ200 በላይ ህዝብ ሲያልቅ ትንፍሽ ያላሉት ግሰለብ «እንኩዋን ደስ አላችሁ» በማለት ለአነመለስ የመጀመሪያው እውቅና ሰጪ በመሆናቸው መላው የሀገሪቱ ህዝቦች በግለሰቡ በጣም እንደተበሳጩና አሁንም የኢህአዴግ አባል ተብሎ ቅፅል ስም ወጥቶላቸው እንደነበረ የገለፁት ምንጮቹ የስራ ጊዜያቸውን አጠናቅቀው ሲሄዱ ለመኖሪያ ይሆናቸው ዘንድ ኪሎ ግራሙ ያልታወቀ ወርቅ በስጦታ መልክ ከወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ማግኘታቸውን ምንጮቻችን አጋልጠዋል።

ለአፍሪካ ሕዝቦች ቅንጣት ታክል አገልግሎት ያልሰጡት እኚሁ አልፋ ኦማር ኮናሬ በኢትዮጵያ ህዝብና ሀብት በነመለስ አማካኝነት ሲንደላቀቁ የቆዩ ሲሆን፣ በሕዝቡ ላይ በሚደርሰው በደልና ግፍ ዙሪያ ወያኔን አንድም ቀን ሳይወቅሱና ሳይቃወሙ የእነ መለስን ትዕዛዝ ተግባራዊ ሲያደርጉ የነበሩ በመሆናቸው ሽልማቱ በአብሮነታቸው ግዜ ስላደረጉት የተከፈለ ውለታ ስለሆነ አይበዛባቸውም የሚሉም የዲፕሎማት ምንጮች ይገልፃሉ።

ባልንጀሬ ብሎ የሰረቁትንም ቢሆን አካፍሎ መብላቱ ምን ያህል ውለታቸው አጥንት ሰባሪ እንደነበር የሚያሳይ ቢሆንም ወርቁ ባሌስትራ ቢሆንስ

ኮናሬ እንባቸውን ቢያፈሱ አገራቸው ማሊ በጎርፍ ብትጠቃስ..እሳቸውስ ወርቅ መሆኑን ሲያዩ ቅድሚያ ይመርመር አለማለታቸው

ቢያንስ ኦርጂናሉ ከብሄራዊ ባንክ ይልቅ በእነመለስ እጅ መቀመጡን ስለሚያምኑ አልተጠራጠሩም የሚሉትን ወገኖች ሃሳብ ማድመጥ ተገቢ ሳይሆን አይቀርም ምክንያቱም በኑሮ ውድነት እና በግፍ ስቃይ የቆሰለም ቢሆን ሃሰት አይነገርምና ነው

የወያኔው ቡድን የሚያደርገውንና የሚሰራውን እያጣ በመጣበት ወቅት በሕዝቡ ላይ የሚያደርሰውን በደል ከቀን ወደ ቀን እያስፋፋ ሰሞኑን ደግሞ ሕዝቡ በትራንስፖርት እጦት እንዲሰቃይ ማድረጉ ታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመንንዣ ትንስፖርት ጋር ያልተጣጣመ ሲሆን፣ ይህንኑ ችግር በጥቂቱም ቢሆን ይቀርፋሉ ተብለው በታክሲ አገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩትን ኮድ 3 የለጠፉ ሚኒባሶች ከስራቸው ማገዱ ታውቋል፡፡

ከሰኞ ሚያዚያ 13 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳይሰጡ የተከለከሉት እነዚሁ መኪኖች ያለ አገልግሎት ተገትረው እየዋሉ ሲሆን፣ ሕዝቡም በትራንስፖርት እጦት እየተንገላታ መሆኑ ታይቷል፡፡

የወያኔው ቡድን ይህንን እርምጃ የወሰደው በቅርቡ ከቻይና ያስገባቸው ሚድባስ የተባሉት ጉልበት አልባ መኪኖች የሚገዛ ስለጠፋ እንዲሸጡለት ለማድረግ አስቦ ሲሆን፣ በአሁን ሰዓት ከ300 በላይ መኪኖች ገዥ አጥተው ገርጅ በሚገኘው አንበሳ የከተማ አውቶብስ ጋራዥ ውስጥ ተገትረው እንዳሉና ስራም ላይ ተሰማርተው ከሚገኙት ግማሽ ያህሉ በዋሊያ አገር አቁዋራጭ አውቶብስ ጋራዥ ውስጥ ተገትረው እንደቆሙ ተዘዋውሮ የተመለከተው ዘጋቢያችን ሪፖርት ያስረዳል፡፡

ወያኔ በግምትና በነሲብ እንጂ በእቅድና ፕሮግራም የማይንቀሳቀስ ደንባራ ቡድን በመሆኑ ከሀገሪቷ መልክአ ምድር ጋር የማይጣጣሙ ቻይና ሰራሽ መኪና በውድ ዋጋ ካስገባ በኋላ ዛሬ ሲፈተሹ በጣም ለስራ የማይመቹ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን ከብሔራዊ ባንክ የሕዝብ ገንዘብ 136.5 ሚሊዮን ብር ወጪ አድርጐ ግዥ የፈፀመ ቢሆንም ገዥ አጥተው በመቆማቸው መክሰሩን ያረጋገጠው ወያኔ እንደገና ሕዝቡ በትራንስፖርት ችግር እንዲንገላታ እያደረገ መሆኑ እጅግ አሳፋሪ ተግባር መሆኑንም ሕዝቡ በቁጭት እየገለፀ ይገኛል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሚያዝያ 13 ቀን 2000 ዓ.ም በአይሱዙ ከጐጃም ወደ አዲስ አበባ ከተማ ሲገባ አዲሱ ገበያ ላይ ሲደርስ የነፍስ ወከፍ መሣሪያና ፈንጅ ተያዘ በሚል ሰበብ የፌዴራል ፖሊሶች ሕዝቡን የቁም ስቅል እያሳዩት መሆኑ ታውቋል፡፡

በተለይም በእንጦጦ ፍተሻ ላይ ተመድበው ሲሰሩ የነበሩ 6 ፖሊሶች የዕለቱ ተረኛ ናቸው የተባሉትን የወያኔ ደህንነቶች ለጥያቄ ትፈለጋላችሁ ብለዋቸው በዚያው ወስደው ያስቀሩዋቸው ሲሆን፣ እስከ አርብ ሚያዝያ 17 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ የት እንደደረሱ ለማወቅ እንዳልተቻለና ቤተሰቦቻቸው እያለቀሱ በፍለጋ ላይ መሆናቸውን ለግለሰቦቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ወያኔ እንኩዋን ለሕዝብ የስልጣን እድሜዬን ያራዝሙልኛል ብሎ ሲኮራባቸው በነበሩት የፌዴራል ፖሊሶች ላይም እምነት የሌለው ቡድን መሆኑን ያሳየበት ነው ያሉት አንድ መኮንን እኛም የግድ ስለሆነ እንጂ ስራ መስራት የሚቻልበት ደረጃ ላይ አይደለንም ባልተደረገና ባልተፈጠረ ታሪክ እራሳቸው በሰሩት ድራማ መልሰው ሕዝቡን እያሰቃዩት ነው ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ድራማው መሰራቱ ከታወቀ አብሮ ከመሳቅ እና የሚያለቅስ ሰላማዊ ዜጋ እያደኑ የድራማው መጫወቻ እንዲሆን ማድረግ የማን ፈንታ ነበር

የሚያሳዝነው በደህንነትና በፖሊስ በጦር ሰራዊት ውስጥ ያላችሁ ወገኖች በእነማን ላይ ምን እየደረሰ እንደሆነ አልሰማችሁም ? እንዴት አንድ ጠባብ አናሳ ቡድን በመላ የህዝብ ልጆች ላይ እንዲህ

ይቀልዳል ? የነገስ እጣ ፈንታችን ምንድን ነው ብሎ ማሰብ እና ሳይመሽባችሁ መላ ማለቱን አትዘንጉ በማለት አንድ የፖሊስ መኮንን የነበሩ አሁን ወደ ደህንነት የተዛወሩ መኮንን ለዘጋቢያችን አስተያየት ሰጥተውታል